MONTGOMERY COLLEGE

ከ: Krista Leitch Walker
Vice President of Human Resources and Strategic Talent Management

**ጉዳዩ፡-** **ካምፓስ ውስጥ ለመስራት የ COVID-19 የደህንነት ቅድመ ጥንቃቄዎች**

ወደ ካምፓሱ እንኳን በደህና መጡ! ከሁሉም በማስቀደም፣ ኮሌጃችን የሠራተኞቻችንን እና የተማሪዎቻችንን ደህንነት ለመጠበቅ በቁርጠኝነት እንደሚሰራ ለማረጋገጥ እንወዳለን። COVID-19 ን ጨምሮ፣ የተለያዩ ዓይነት በሽታዎች ላይ ተጋላጭነትን እና ስርጭትን ለመቀነስ የሚያግዙን ተከታታይ የደህንነት ቅድመ ሁኔታዎች እና ፕሮቶኮሎችን በተግባር ላይ አውለናል። እነዚህም የሚያካትቱት አዳዲስ የማጽዳት ቅድመ ሁኔታዎች እና የቦታ አቀማመጦች፣ ለሠራተኞቻችን ትምህርት እና ስልጠና መስጠት፣ ካምፓስ ውስጥ የመግቢያ አዲስ መመሪያዎች ናቸው።

ከዚህ ቀደም አስቀድመው እንደሚያውቁት፣ በመላው የመከር ወቅት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አብዛኛዎቹ የኮሌጁ ካምፓሶች እና መገኛ ቦታዎች ቦታው ላይ በመገኘት ለሚሰጡ ትምህርቶች እና አገልግሎቶች እንደተዘጉ ይቆያሉ። በጣም የተመረጡ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ሕንፃዎች ብቻ ለተማሪዎች፣ ለፋካልቲ ሠራተኞች ይከፈታሉ ምክንያቱ ደግሞ የግድ በግል መገኘት የሚያስገድዱ የትምህርት ዓይነቶች ወይም ሌሎች የአሰራር አስፈላጊነቶች በመኖራቸው ነው።

በተሰጥዎት ሚና እና ሃላፊነት መሰረት፣ በመከር ወቅት የኮሌጁ አንዱ ካምፓስ ላይ በስራ ገበታዎ ላይ ተመልሰው ተገኝተው እንዲሰሩ ተመድበዋል።

የኮሌጃችንን ማህበረሰብ ደህንነቱ መጠናቀቁን ለማረጋገጥ፣ ከታች የተጠቀሱትን ቅድመ ጥንቃቄዎችን እና ፕሮቶኮሎችን እንዲያከብሩ ለፋካልቲ ሠራተኞቻችን እና ለሠራተኞቻችን እየጠየቅን ነው።

## ወደ ኮሌጅ ቅጥር ግቢ የመመለሻ ቅድመ ዝግጅት

1. ***ወደ ሥራ ገበታቸው ለሚመለሱ ለሁሉም የኮሌጅ ሠራተኞች የሚጠበቅባቸውን የሚከተለውን ኦንላይን የ COVID-19 ደህንነት ስልጠና ይውሰዱ።*** በባለሙያ ልማት ማስተማሪያ አስተዳደር ስርዓት፣ ኤምሲ ለርንስ በኩል [ይሄንን ስልጠና እንዴት እንደሚያገኙ](#) የሚለውን ይመልከቱ።

    *ለሁሉም ሠራተኞች፡-*
    - ለሠራተኞች ወደ ካምፓስ ዌቢናር ይመለሱ፡- የእርስዎ የስራ ቦታ ላይ የ COVID-19 ለውጦች

ለሁሉም የበላይ ተቆጣጣሪዎች፡- ለሠራተኞች ከላይ ከተጠቀሰው ከዌቢናር በተጨማሪ፣ የበላይ ተቆጣጣሪዎች የሚከተለውን

ስልጠና ማጠናቀቅ አለባቸው፡- ከመስከረም 11, 2020 በፊት ማሟላት ዱጠበቃል

- o ለበላይ ተቆጣጣሪዎች ዌብናር መመሪያ፡- የእርስዎ የስራ ቦታ ላይ የ COVID-19 ለውጦች

2. **በግል እና በድንገተኛ ጊዜ የሚገኙበት መረጃ የቅርብ መሆኑን ለማረጋገጥ ወርከዴይ ላይ በመለያዎ ይግቡ።** የእርስዎን [የግል](#) እና [የድንገተኛ ጊዜ የሚገኙበት](#) መረጃ እንዴት እንደሚያዘምኑ መመሪያዎቹን ይመልከቱ።

3. **ሙሉ ለሙሉ እና በጥንቃቄ የ** [*ከ ጁላይ 1 ቀን፣ 2020 ጀምሮ በስራ ቦታ ተገኝቶ መስራት ላይ የወጡትን የሞንትጎመሪ ኮሌጅ ጊዜያዊ መስፈርቶች*](#) እና የመከር 2020 አስፈላጊ የጤና እና ደህንነት መረጃን ያንብቡ።

## ወደ ኮሌጁ የሚገኙበት ቦታ ሪፖርት ከማድረግዎ እና ከመግባትዎ በፊት

1. **ከቤትዎ ከመውጣትዎ በፊት፣ ሪፖርት የሚያደርጉበት የኮሌጁ መገኛ ቦታ ላ በየቀኑ [ዕለታዊ COVID-19 ምልክቶች የራስ ግምገማ](#) ያጠናቅቁ።** በምላሾቹ መሰረት የእርስዎ ማሰሻ ውስጥ እና በኢሜይልዎ በኩል ውጤቶቹን ይቀበላሉ (አረንጓዴ ወይም ቀይ X ምልክት ያለበት)። እባክዎን ግምገማው ላይ የተገኘው መረጃ እንደማይቀመጥ፣ እንደማይከማች ወይም በኮሌጅ ተይዞ እንደማይቀር ያስታውሱ።

2. **ምልክቶቹ የሚታይብዎት ከሆነ፣ በቤት ውስጥ ይቆዩ!** ቅድመ ምርመራው ላይ የተዘረዘሩት ማንኛውም ምልክቶች ላይ "አዎ" የሚል ምላሽ የሰጡ ከሆነ፣ ወዲያውኑ፣ በተያዘልዎት የስራ መርሀግብር መሰረት ወደ ስራ ሪፖርት አያድርጉ።
የበላይ ተቆጣጣሪዎን ያሳውቁ እና የእርስዎን ሕክምና አገልግሎት ሰጪዎን ያግኙ። ምልክቶችዎ ልክ እንደ አለርጂዎች ወይም ጉንፋን የመሳሰሉ፣ ሌሎች ሁኔታዎች የተነሳ የመጡ ናቸው ቢለው ቢያስቡም፣ አሁንም ቢሆን ይሄንን መመሪያ መከተል እና በቤት ውስጥ መቆየት አለብዎት።

3. **የፊት መሸፈኛ ይዘው እንደመጡ ያረጋግጡ።** አፍንጫን፣ አፍን እና አገጭን የሚሸፍኑ የፊት መሸፈኛዎች ሁልጊዜ የኮሌጁ ካምፓስ ውስጥ እና ሌሎች ቦታዎች ላይ መለበስ አለባቸው። የፊት መሸፈኛ የሌለዎት እንደሆነ፣ ከታች ንጥል #4 ላይ የተጠቀሱት የፍተሻ ቦታዎች አንዱ ላይ የ MC ማስክ ማግኘት ይችላሉ።

4. **በየቀኑ ወደ ኮሌጁ የሚገኙበት ቦታ ሪፖርት በሚያደርጉበት ሰዓት ካምፓስ ላይ ልክ እንደደረሱ የሕዝብ ደህንነት ጋር ይፈተሹ።** የኢሜይል ደረሰኙን ከአረንጓዴው ቼክ እና የጊዜ ማህተም ጋር ለማሳየት ይዘጋጁ። በተጨማሪም በቦታው ላይ የወረቀት ኮፒዎች ይገኛሉ። የ MC ማስክ ማግኘት የሚያስፈልግዎት ከሆነ፣ ደረሰኝ እንዲቆረጥልዎት ለመፈረም ይዘጋጁ። የሚከተሉት አሁን ያሉት የፍተሻ ቦታዎች ናቸው፡-

ሮክቪል ካምፓስ **(Rockville Campus)**

- ጉዴሊስክ የቴክኒክ ትምህርት ተቋም (Gudelsky Institute for Technical Education (GU))
- ሳይንስ ዌስት (Science West) (SW)

ታኮማ ፓርክ/ ሲልቨር ስፕሪንግ ካምፓስ **(Takoma Park/Silver Spring Campus)**

- የጤና ሳይንስ ማዕከል (Health Sciences Center) (HC)
- ካፍሪትዝ የስነጥበብ ማዕከል (Cafritz Arts Center) (CF)

**ጀርመንታውን ካምፓስ (Germantown Campus)**

- ባዮሳይንስ ትምህርት ማዕከል (Bioscience Education Center) (BE)

**ሴንተራል ሰርቪስስ ህንፃ (Central Services Building) (CT)**

- የሕዝብ ደህንነት የመረጃ ዴስክ

እባክዎን የፍተሻ ቦታው ላይ ለመግባት ሲሞክሩ መዘግየት ያለ ከሆነ ተጨማሪ ጊዜ ለራስዎ መስጠት እንዳለብዎት ያስታውሱ። እንደዚሁም፣ በካምፓሱ እና በህንፃው አስፈላጊነት መሰረት፣ የፍተሻ ቦታዎች ሊቀየሩ ይችላሉ። ለውጦች በማሳወቂያዎች፣ በማስታወቂያ አርማዎች እና ሌሎች መግባቢያ መንገዶች በኩል ይተላለፋሉ።

## የኮሌጁ ቦታ ላይ በመስራት ወቅት

ማንኛውም ኮሌጁ የሚገኝበት ቦታ ላይ ሪፖርት ሲያደርጉ ጊዜ፣ የሚከተሉትን የደህንነት መስፈርቶች እና ቅድመ ሁኔታዎች ማክበር ይጠበቅቦታል።

1. **ምልክቶቹ የሚታይብዎት እና የህመም ስሜት መሰማት የጀመርዎት ከሆነ የስራ ቦታውን በፍጥነት ለቀው ይውጡ።** እባክዎን የእርስዎን የበላይ ተቆጣጣሪ ወዲያውኑ ማሳወቅ እንዳለብዎ እና ከእርስዎ የጤና እንክብካቤ ሐኪምን እንዳገኙ እርግጠኛ ይሁኑ። በስራ ቦታ ላይ ሆነው ምልክቶቹን ማየት መጀመርዎን ለእነርሱ ለማሳወቅ environmentalsafety@montgomerycollege.edu ላይ ኢሜይል ይፃፉ።

2. **በስራ ቦታ ላይ በሚሰሩበት ሰዓት የፊት መሸፈኛ ያድርጉ።** እባክዎን ለተጨማሪ መረጃ MC ሠራተኞች የፊት መሸፈኛ መሸፈኛ መመሪያን ይመልከቱ።

3. የማህበራዊ ርቀት መጠበቅ ሕግን ያክብሩ እና በእርስዎ እና በማንኛውም ሰው መካከል ቢያንስ 6 ጫማ ያህል ርቀት ይጠብቁ። 6 ጫማ ወይም ከዚያ በላይ ርቀት መጠበቅ ያልቻሉ ከሆነ፣ ከቦታው ላይ ራስዎትን ያርቁ።

4. **መደበኛ የሆነ እጅ መታጠብን እና/ወይም እጅ ሳኒታይዝ ማድረግን ያዘውትሩ።** እጅዎን ቢያንስ ለ 20 ሰከንዶች ያህል በሙቅ ውሃ እና በሳሙና ይታጠቡ። የእጅ ሳኒታይዘር ማሽኖች የሕንፃዎቹ መግቢያ፣ ትራፊክ ያለበት ቦታ እና የመማሪያ ክፍሎች ላይ ይቀመጣሉ።

5. **በኮሌጁ የሚቀርቡትን ሁሉንም የጤና እና የደህንነት ፕሮቶኮሎች ያክብሩ እና መከታተለዎን ይቀጥሉበት።** ስለ COVID-19 ግንዛቤዎን ማሳደግ የጋራ ሃላፊነት ነው። ኮሌጁ ከእኛ ብሔራዊ፣ የግዛት፣ እና የካውንቲ የጤና እንክብካቤ ሰጪ ባለሙያዎች በተከታታይ አዳዲስ የጤና እና የደህንነት እርምጃዎችን እየተከታተለ ይገኛል። የበለጠ ተጨማሪ መረጃ በሚገኝበት ጊዜ፣ እነዚህን መመሪያዎችን እንቀይራቸዋለን እና ስለ አዲሱ ለውጥ እርስዎን እናሳውቆታለን። እባክዎን ኢሜይሎችን፣ የማህበራዊ ሚዲያ መጣጥፎችን፣ እና በቅጥር ግቢው ውስጥ የሚለጠፉ ጽሁፎችን እና ማስታወቂያዎችን ጨምሮ፣ የኮሌጁን የመግባቢያ ጽሁፎችን ሙሉ ለሙሉ እና በጥንቃቄ በማንበብ ድርሻዎን ይወጡ።

6. **ማንኛውም ሊከሰት የሚችል COVID-19 ተጋላጭነትን ወይም ሌሎች የጤና እና የደህንነት ስጋቶችን በሚከተለው አድራሻ ሪፖርት ማድረግዎን ያረጋግጡ፡- [environmentalsafety@montgomerycollege.edu](mailto:environmentalsafety@montgomerycollege.edu)**
   ሁሉም ሪፖርቶች በሚስጥር ይያዛሉ። የምላሽ እርምጃዎች በ Occupational and Environmental Safety Office ቢሮ በኩል ይተገበራሉ።

7. **ከሜሪላንድ COVID-19 የተያዘ ሰው መከታተያ ጥሪቶች በሚወከሉ ተወካዮች በኩል ለሚመጡ ማንኛውም ጥሪዎች ምላሽ ይስጡ እና ይሳተፉባቸው።** የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል የተያዘ ሰውን መከታተል ወሳኝ ተግባር ነው። ከ 240-466-4488 ወይም MD COVID በኩል ስልክ ከተደወለልዎት፣ እባክዎን የስልክ ጥሪውን ያንሱ እና ከእርስዎ የሚጠበቅብዎትን ማንኛውም መረጃ ይስጡ።

በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት ስለ ጤና እና ደህንነት ምርጥ የሆኑ ተግባራትን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የሚከተሉትን ድረገጾች እንዲጎበኙ እናበረታታዎታለን፡-

[Centers for Disease Control - Coronavirus (COVID-19)]

[Montgomery County Government - COVID-19 Information Portal]

[Montgomery College - Coronavirus: What You Need to Know]

እባክዎን ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ወይም ስጋት ያለዎት ከሆነ፣ እባክዎን ከታች የተጠቀሰውን የእርስዎን የሰው ሀብት መምሪያ የውስጥ አማካሪ [Human Resources Internal Consultant (HRIC)] ያነጋግሩ፣ ወይም በሚከተለው ኢሜይል አድራሻ ይላኩ HRSTM@montgomerycollege.edu ።

**ሮክቪል ካምፓስ እና ጌተርስበርግ የንግድ ስልጠና ማዕከል (Rockville Campus and Gaithersburg Business Training Center)**
ካርላ አመርማን (Carla Ammerman)
301-852-0029

**ማእከላዊ አገልግሎቶች፣ ጀርመንታውን ካምፓስ፣ እና በሮክቪል ካምፓስ ላይ የተቋማት እና የሕዝብ ደህንነት ቢሮዎችን (Central Services, Germantown Campus, and the Offices of Facilities and Public Safety at Rockville Campus)**
ለስሊ ጆንስ (Leslie Jones)
301-852-0095

**ታኮማ ፓርክ/ሲልቨር ስፕሪንግ ካምፓስ እና ዌስትፊልድ ሳውዝ (Takoma Park/Silver Spring Campus and Westfield South)**
አሽሊ ሮበርትስ (Ashley Roberts)
301-852-0213

ተማሪዎቻችንን እና ማህበረሰባችንን ማገልገል እና ድጋፍ መስጠት ላይ ስለሳዩት ቁርጠኝነት እና ስለከፈሉት ዋጋ እናመሰግንዎታለን።

ግልባጭ፡ Dr. Monica Brown, Senior Vice President for Student Affairs
Dr. Sanjay Rai, Senior Vice President of Academic Affairs
Ms. Donna Schena, Senior Vice President of Administrative and Fiscal Services
Mr. David Sears, Senior Vice President of Advancement and Community Engagement